**የቅንጅት ዓለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ምስረታን በተመለከተ ከቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ**

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በኢትዮጵያ የሚካሄደዉን የህዝብ ትግል አቅጣጫና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የመምራት ታሪካዊ ሃላፊነት አለበት:: የኢህአዴግ መንግስት የፓርቲዉን መሪዎች በማሰር የትግሉን ሂደት ለማክሸፍ ጥረት ቢያደርግም ቅንጅት ባለዉ የህዝብ ድጋፍና የለዉጥ ፍላጎት ላይ በመመስረት የህዝቡን ትግል የማቀነባበር ተግባሩን ቀጥሎአል::

በመሪዎቻችን መታሰርና በኢህአዴግ ጸረ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የፖለቲካ አመራር ክፍተት መዝጋት አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነዉ:: በዚህ መሰረት ትግሉን በበለጠ ጥንካሬ ለመምራት ዓለም ዓቀፍ የፖለቲካ ትግል አመራር ኮሚቴ ለማዋቀር መመሪያ ወጥቶአል::

የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ የስራ አመራር ዛሬ ግንቦት 19 ቀን 1998 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ተሰብስቦ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶአል:: በዚሁ መሰረት የወጣዉ መመሪያ ወቅታዊ መሆኑን ቢቀበልም በሥራ ላይ ለማዋል እነዲቻል በአሰራር፡ በሥራ ተዋረድ ተጠሪነት እንዲሁም ከሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ ጋር የሚኖረዉ የግንኙነት ጥያቄን በሚመለከት ማብራሪያ መመሪያም በአስቸኩዋይ እንዲጠየቅ ወስኗል::

የቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴ
ዋሺንግተን ዲሲ
ግንቦት 19 ቀን 1998 ዓ.ም

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com